ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ከአሜሪካን ድምጽ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ በጽሁፍ እንደሚከተለዉ አቀርበነዋል።

*ሰለሞን ክፍሌ - ጤና ይስጥልኝ ፕሮፌሰር መስፍን እንደምን ዋሉ ?*

ፕሮፌሰር መስፍን - ጤና ስጥልኝ ሰለሞን እንደምን ዋልክ ?

*ሰለሞን ክፍሌ - እስቲ በአጭሩ ምን እንደተፈጠረ ይግለጹልን ዛሬ።*

ፕሮፌሰር መስፍን - ዛሬ የሆነዉ ጠዋት ፓስተር ዳንኤል ቢሮ ብርቱካንና እኔ ከፓስተር ዳንኤል ጋር ሆነን ስንነጋገር ቆይተን ነበር። ስንወጣ ከግቢዉ በሩ ላይ ቆመን እየተነጋገርን እያለ አንድ አራት የሚሆኑ መኪናዎች መጡ። ተንደረደሩና ሰዎቹ አንድ አሥር የሚሆኑ ሰዎች ናቸዉ። እርሷን ከበቡና ይዘዉ ይገፏት ጀመር። «ለምን ትገፏታላቹህ ? ሕጋዊ ሥርዓት ካለ አንድ ወረቀት አንድ ሰዉ ይዞ መጥቶ ሊወስዳት ይችላል» ስል ጊዜ በስድብ ናዳ ወረዱብኝ። እርሷን እየገፋፉ ሲወስዱ «እረ ባካቹህ ይሄ ትክክል አይደለም» ስላቸዉ አንድ ጀግና ወያኔ ወታደር በያዘዉ ጠመንጃ ሰደፍ የኋሊት እዚህ ፊኛዬ ላይ መታኝ። አልወደኩም ግን ተንገዳገድኩና ጫማዬም ወለቀ። እዚህ እታች ቋንጃዬንና ባቴን እስር አድርጎ ይዞኝ በኃይል ያመኛል አሁን። ሐኪም ጋር ሄድኩና አሳየሁት። «በዚያ የሚመጣ ሥር የሚያልፍ አለና ኩላሊትህን ደግሞ ነክቶት እንደሆነ ነገ ትመረመራለህ» ብሎኝ ተመለስኩኝ።

*ሰለሞን ክፍሌ - ወ/ት ብርቱካን አሁን ወዴት እንደተወሰዱ ይታወቃል ?*

ፕሮፌሰር መስፍን - ከመሸ በኋላ የሰማሁት ቃሊቲ ወስደዉታል ሲሉ ነዉ።

*ሰለሞን ክፍሌ - ለርሳቸዉ በፌደራል ፖሊስ የተሰጣቸዉ የጊዜ ገደብና ማስጠንቀቂያ ካበቃ በኋላ ትላንት ላናግራቸዉ ፈልጌ ለዛሬ ሰጥተዉኝ ነበር የተለያየነዉ። አሁን መልሼ ሰደዉል ይሄንን ዜና ሰናሁ። እርስዎ ጉዳዩን በሚገባ ያዉቃሉ ብዬ አምናለሁ፣ ፕሮፌሰር መስፍን የፖሊሱ ማስጠንቀቂያ ገደብ ምንጩ ምንድን ነዉ ይላሉ ።*

እርሷ የሰጠችዉ መልስ የተናገረችዉ ነገር ምንም ስህተት የለበትም። በእዉነት ለእዉነት መመስከር የሚችሉ ሰዎች ደግሞ ቢኖሩ ፕሮፌሰር ኤፍሬምም ፓስተር ዳንኤልም ሌሎችም አሉ። እርሷ በሽምግልናዉ በኩል ተኬዶ ይቅርታ ጠይቅን ነዉ ያለችዉ። በሕጋዊ ሥርዓት ግን ሌላ አይነት መንገድ ነዉ ያለዉ። አንደኛ መጀመሪያ ዉሳኔ መስጠት አለበት። ፍርድ መፈረድ አለበት።ይቅርታ ለመጠየቅ። እና ይሄ የተጀመረዉ ገና ገና ዉሳኔ ብይንም ሳይሰጥ ነዉ። ፍርድ ከተፈረደ በኋላ እሥረኞቹ ምንድን ነዉ የሚያደርግት ቃሊቲ እንዳየነዉ ? ፍርም አለ። ይቅርታ መጠየቅ ሲፈልጉ ፎርም ይሰጣቸዋል። የይቀርታ ኮሚቴ እሥር ቤት ዉስጥ አለ። ፍሮም ይሰጣቸዋል። አንድ አሥር ገጽ ይሆናል። ያንን ይሞላሉ። ያንን ሞልተዉ ይመልሳሉ። ሲመልሱ ለየቀበሌዉ ከጎርቤቶች ከሰዎች ከሚያወቋቸዉ ሰዎች አጣርቶ አስተያየት ሰብስቦ እንደገና መልስ ለእሥር ቤቱ ይላካል። እሥር ቤቱ ያንን ካየ በኋላ ወደ ይቅርታ ቦርድ የሚልከዉን ይልካል። የሚያስቀረዉን ያስቀራል። ይኼ ነዉ በይቅርታ ኮሚሽኑ የሚሄደዉ። እርሷ በሽምግልናዉ ነዉ የሄድነዉ ይቅርታ የጠየቅነው ነዉ ያለችዉ።

ይሄ ትክክል ነዉ። ማንም የሚከደዉ ነገር አይደለም። እዚህ ነዉ እንግዲህ «ይሄንን አንቺ በሕጋዊ መንገድ ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል።» ያሉት። በሕጋዊዉ ሁለቱም ሕጋዊ ሆኗል ለነገሩ። ይሄም ሕጋዊ ነዉ። በይቀርታ ኮሚሽን በኩል ሄደ። ፕሬዘዳንቱ ጋር ደርሶ ነዉ ይቅርታዉ ተሰጠ የተባለዉ። እና ሕጉ ነጋሪት ጋዜጣ የሚያዘዉን ሕጋዊ ሥርዓት አልተከተለም። የኛ በሌላ በኩል ነዉ የሄደዉ ነዉ እርሷ የምትለዉ። ደግሞ ሕጉን በሚገባ ታዉቀዋለች።

*ሰለሞን ክፍሌ - አዎ የሕግ ባለሞያ በመሆናቸዉ ያዉቃሉ !*

የሕግ ባለሞያ ነች። ምንም ይቅርታ መጠየቋን አልካደችም። ችግሩ እንደዉ ዝም ብሎ «ኢያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ” የሚለዉ አይነት ነገር ነዉ።ያም ከሆነ ሥርዓት ባለዉ መንገድ ሰዎቹ አሉ። እነዚያ ሰዎች ፕሮፌሰር ኤፍሬም አለ።

ፓስተር ዳንኤል አለ። አትሌት የታወቀዉ ኃይሌ አለ። እነዚህ ሁሉ ያዉቃሉ። የሆነዉን ነገር የተደረገዉን ነገር። እና ምንም የሚያስቸግር ነገር አልነበረም። እንደዚህየሚያደርስ የሚያቃቀር ዱላም ጋር የሚያደርስ ነገር የለም። ግን እንግዲህ ፖሊስ ሆኗል ሁሉን ነገር የሚያደርገዉና እየገባን በመሆኑ ይመስለኛል እዚህ ጋር የደረሰኡት።

*ሰለሞን ክፍሌ - ፕሮፌሰር መስፍን ለሰጡኝ ማብራሪያ አመሰግናለሁ። እንዳሉት ሽማግሌዎቹንም ፈልገን ለማነጋገርና ማብራሪያ እንዲሰጡን ለማድረግ እንሞክራለን። እንደጋና ለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ። ደህና ያምሹ።*

ፕሮፌሰር መስፍን - እግዚአብሄር ይስጥልኝ